

# HOMEBUILDERS®

## ከፍተኛ የቤተሰብ ጥበቃ አገልግሎቶች (IFPS)

### ስለ አገልግሎቱ

Intensive Family Preservation Services (ከፍተኛ የቤተሰብ ጥበቃ አገልግሎቶች፣ IFPS) ቤተሰብ ተኮር፣ በባህሪ ማሻሻያ ላይ የተመሠረተ እና በቤት ውስጥ የሚሰጥ የምክርና የድጋፍ ፕሮግራም ነው። HOMEBUILDERS® ልጆች ከቤተሰብ ውጪ እንዳይወጡ ለመከላከል ከማደጎ እንክብካቤ (foster placement) በኋላ ቤተሰቦችን እንደገና ለማቀላቀል የIFPS አገልግሎት ለሚያስፈልጋቸው ቤተሰቦች የተዘጋጀ በማስረጃ ላይ የተመሠረተ ሞዴል ነው። ይህ ሞዴል በልጆች ደህንነት፣ በቀውስ ጊዜ እርዳታ መስጠት፣ ከማህበረሰብ ሀብቶች ጋር ማገናኘት እንዲሁም ወላጆች/አሳዳጊዎች ችግር ፈቺነትን እና የዕለት ተዕለት የኑሮ ክህሎቶችን እንዲማሩ በማስተማር ላይ ያተኮረ ነው። አገልግሎቶቹ በአብዛኛው ለአራት ሳምንታት የሚቆዩ ሲሆን፣ በዚያ ወቅት ከአማካሪ ጋር በአማካይ 38 ሰዓታት አካባቢ የሚፈጅ ነው።

*አገልግሎቶቹ ችግሮቹ በሚከሰቱበት እና በመጨረሻም መፈታት በሚገባቸው ተፈጥሯዊ አካባቢ (በቤት፣ በማህበረሰብ ውስጥ) የሚሰጡ ይሆናል።*

### አገልግሎቱ የሚጠቅመው ማንን ነው?

HOMEBUILDERS® ከልደት እስከ 18 ዓመት ዕድሜ ያሉ ልጆች ላሏቸው የስጋ፣ የጉዲፈቻ እና የዝምድና ቤተሰቦች የተዘጋጀ ነው።

### የአገልግሎቱ ዋና ዋና ነጥቦች

- በቀን 24 ሰዓት እና በሳምንት 7 ቀን ዝግጁ እንዲሁም ተለዋዋጭ የቤት ጉብኝት መርሃ ግብ
- ቴራፒስቶች እና ቤተሰቦች አገልግሎቱ በጣም በሚያስፈልግበት እና ከፍተኛ ውጤት በሚያመጣበት ሰዓት፣ በሳምንት ከሶስት እስከ አምስት ጊዜ ይገናኛሉ።
- ቤተሰቦች ፍላጎቶቻቸውን፣ ጥንካሬዎቻቸውን እና ግቦቻቸውን እንዲለዩ የሚረዳ አጠቃላይ እና በይነተገናኝ ግምገማ።
- የተማሯቸው ክህሎቶች፣ አገልግሎቶቹ ካበቁ ከረጅም ጊዜ በኋላም ቤተሰቦች ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ።
- ቤተሰብ በሁሉም የጣልቃ ገብነት ዘርፎች እና በጋራ አገልግሎት እቅድ ላይ በንቃት ይሳተፋል።
- አገልግሎቶቹ ቤተሰቡን በማህበረሰቡ ውስጥ ካሉ መደበኛ እና ተፈጥሯዊ የድጋፍ ምንጮች ጋር ያገናኛሉ።

### ድጋፍ:-

**ልጆች እና ቤተሰቦች የልጆችን ደህንነት የሚደግፉ፣ የጥቃት ወይም የቸልተኝነት አደጋን የሚቀንሱ፣ የቤተሰብ መረጋጋትን የሚያረጋግጡ ወይም ደህንነቱ የተጠበቀ መገናኘትን የሚያመቻቹ ቁሳቁሶችን እንዲያገኙ ለመርዳት፣ እስከ $500 ሊገኝ ይችላል።**

Washington State Department of
CHILDREN, YOUTH & FAMILIES

*DCYF ለሁሉም ለፕሮግራሞቹ እና አገልግሎቶቹ ዘር፣ ቀለም፣ ጾታ፣ ሃይማኖት፣ እምነት፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የዜግነት ሁኔታ፣ የዜግነት ወይም የኢሚግሬሽን ሁኔታ፣ ዕድሜ፣ የጾታዊ ዝንባሌ ወይም የጾታ ማንነት፣ እድሜ፣ የውትድርና እና የመከላከያ ሁኔታ፣ እንደ ጡት የምታጠባ እናት ሁኔታ ወይም የምንም አይነት አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ ወይም የአዕምሮ እክልን በማየት እና የውሻ መመሪያ ወይም የአገልግሎት እንስሳ በመጠቀም አያዳላም እንዲሁም እኩል ተደራሽነትን ያቀርባል። የዚህን እትም ነጻ ቅጂዎች በአማራጭ ቅርጸት ወይም ቋንቋ ከፈለጉ፣ እባክዎ የDCYF ህዝባዊ ግንኙነቶችን በ1-800-723-4831 ያግኙ ወይም ኢሜይል ወደ* ***communications@dcyf.wa.gov*** *ይላኩ።*

DCYF PUBLICATION PPS_0060 AM (06-2024) Amharic